በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

መጸጉዕ

እንኳን ለዐቢይ ጾም ዓራተኛ ሳምንት በሰላም አደረሳችሁ!!!

የዐቢይ ጾም ዓራተኛ ሰንበት እና ተከትሎት የሚመጣው ሳምንት "መጸጉዕ" ይባላል። "መጸጉዕ" ማለት በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ አምስት ላይ ታሪኩን የምናገኘው ድውይ መጠሪያ ሳይሆን 'በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ የተያዘ በሽተኛ ወይም ሕመምተኛ' ማለት ነው።ጌታችን በመዋዕለ ስጋዌው ካደረጋቸው ነገሮች አንዱ ድውያነ ስጋን በተአምራት ድውያነ ነፍስን ደግሞ በትምህርት መፈወስ ነበርና ጎባጣዎችን አቅንቷል፤ ሽባዎችን ተርትሯል፤ የዓይን ብርሃን የሌላቸውን ብርሃን ሰጥቷል፤ መስማት ለማይችሉት መስማትን ሰጥቷል፤ ለምጻሞችን አንጽቷል። ቅዱስ ያሬድም በደዌ የተያዙ ወገኖች ሁሉን ቻይ የሆነውን ጌታ ተስፋ ያደርጉ ዘንድ ለማስተማር እና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከደዌ የዳኑትን ሰዎች ለማሰብ ይህንን ሳምንት "መጸጉዕ" በማለት ሰይሞታል። በዚህ ሰንበት በቤተ-ክርስቲያናችን የሚሰበከው ምስባክ የሚከተለውን ይመስላል፦ መዝ. 40 ÷ 3-4

እግዚአብሔር ይረድኦ ውስተ ዐራተ ሕማሙ፤ እግዚአብሔር በደዌ አልጋ ሳለ ይረዳዋል፤

ወይመይጥ ሎቱ ኵሎ ምስካቢሁ እምደዌሁ፤ መኝታውንም በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል፤

አነሰ እቤ እግዚኦ ተሣሀለኒ። እኔም አቤቱ ማረኝ እላለሁ።

 ምንባባት፦ ገላ 5 ÷ 1-ፍጻሜ ፤ ያዕ 5 ÷ 14-ፍጻሜ ፤ የሐዋ. ሥራ 3 ÷ 1-12

ቅዳሴ ጊዜ የሚነበበው ወንጌል፦ ዮሐ 5 ÷ 1-25

ይህ መጸጉዕ ለ 38 ዓመት በአልጋ ላይ ሆኖ በደዌ ሲሰቃይ የኖረ ሲሆን በዚህም ምክንያት ዘመዶቹ ሁሉ ሰልችተው ስለተዉት ማንም ረዳት የለውም፤ ዘመድ ያላቸው ወደ ጸበሉ እያስገቧቸው ሲድኑ እየተመለከተ 38 የመከራ ዓመታትንም አሳልፏል። ነገር ግን ሰው ሁሉ የረሳውን የማይረሳው አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያድነው ዘንድ እርሱ ባለበት መንገድ ማለፍን ወደደ፤ አዳነውም። ነገር ግን ጌታ ይህን ሰው ከማዳኑ በፊት ‹‹ልትድን ትወዳለህን›› በማለት ጠይቆታል። እኛም 'ለምን እያወቀ ይጠይቀል?' የሚል ጥያቄ ልናነሳ እንችላለን። በትርጓሜ ወንጌል እንደተብራራው ብዙ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን የተወሰኑትን እንመልከት።

አንድም አምላካችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አላወቂ ሥጋን መዋሀዱን ለማጠየቅ ነው። አንድም እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ፍፁም የሆነ ነፃ ፈቃድን መስጠቱን ለማሳየት ሲል ነው። ክርስቶስ ማንኛውንም ነገር ለሰዎች ሲያደርግ የሰዎችን ፈቃደኝነት ጠይቆ ነው። ለዚህ ነው ሁሉም ሰው ጻድቅ ወይም ሁሉም ሰው ኃጥእ ያልሆነው፤ እግዚአብሔር ፈቃዳችንን አይጋፋምና።አንድም ወደፊት ይህ ድውይ በጌታ ላይ ስለሚመሰክር በሚመሰክርበት ጊዜ 'ያለእኔ ፈቃድ ነው ያዳነኝ' ብሎ እንዳይመሰክር ምክንያት ለማሳጣት ነው። አንድም ጌታችን ትህትናን ያስተምረን ዘንድ ነው። ጌታ የተናገረውን ካስተዋልነው “ልትድን ትወዳለህን?” አለው እንጂ “ላድንህ ትወዳለህን?” አላለውምና።

ጌታችን ይህን ማዳን የፈጸመው በሰንበት በመሆኑ አይሁድ እጅግ ተቃውመዋል፤ እነርሱ ከስራቸው በሰባተኛው ቀን እንደሚያርፉ ሁሉ ልጁንም ከመከራው ዕረፍት በሆነችው በሰንበት ሲያሳርፈው ሊዋጥላቸው አልቻለም። እኛ ግን "በለመለመ መስክ ያሳድረኛል በዕረፍት ውሃ ዘንድ ይመራኛል" እንዳለ ዘማሪው /መዝ 23÷ 2/፤ በቅዱስ ቃሉም "ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለው .... ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ" ያለውን በማመን ክርስቶስ ሰንበት ዕረፍት መሆኗን ዕረፍት በመስጠት እንደተረጐመ እንጂ እንዳልሻረ እንመሰክራለን።እንግዲህ እኛ ክርስቲያኖች ከስጋዊ ደዌአችን ለመላቀቅ የእግዚአብሔርን ማዳን በቤቱ ሆነን ልንጠብቅ ይገባል፤ ላለብን የነፍስ መጻጉዕነት ደግሞ ኃጢአታችንን ለካህን በመናዘዝ ንስሐ ገብተን ስጋ ወደሙን ልንቀበል እና በስጋዊ ደዌ የተያዙ ወገኖቻችንን በመጠየቅ፣ በማስታመም እና በክርስትናቸው በማበርታት አምላካችንን ልናስደስት ያስፈልጋል። እግዚአብሔር አባታችን በቸርነቱ "ታምሜ ጠይቃችሁኛል" በማለት ቃለ ሕይወትን ያሰማን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን!!! አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር!